# ትንቢተ ሶፎንያስ

## ጥናት አንድ ሶፎንያስ 1፡1-18

የጥናት ዓላማ፡- በአንድ በኩል ከእግዚአብሄር የሚገኘውን ነገር ፈልገን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም የምትሰጠውን ፈልገን፤ አንድ እግራችንን በእግዚአብሄር ቤት፤ ሌላውን እግር ደግሞ በዓለም አድርጎ መመላለስ እንደ ይሁዳ ሰዎች የእግዚአብሄርን ቁጣ እንደሚያመጣብን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ለእግዚአብሄር እየሰገዱ፤ በስሙም እየማሉ፤ በሚልኮምም ደግሞ የሚምሉትን፤ እግዚአብሄርን ከመከተል ወደ ኋላ የሚመለሱትን...አጠፋለሁ።" ሶፎ 1፡5-6

1. ትንቢተ ሶፎንያስ 1፡1-18 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቁ1-3 ላይ ስንመለከት፤ ሶፎንያስ ትንቢቱን በተናገረበት ዘመን በይሁዳ ላይ ይገዛ የነበረው ንጉስ ሥም ማን ይባላል? በነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር በባሪያው በነብዩ ሶፎንያስ በኩል አደርጋለሁ ብሎ የሚናገራቸው ነገሮች ምንድናቸው?
2. ከላይ ባየናቸው ቁጥሮች ውስጥ ነገሮችን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲናገር ነበረ የተመለከትነው፤ በቁ4-6 ላይ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ እየለያየ ማስጠንቀቂያውን ሲሰጥ እናያለን፤ በተለይ በቁ5 ላይ አምልኮን አስመልክቶ ሶስት አይነት ሰዎችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሶስት አይነት ሰዎች እነማን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። ህይወትህን ስትመረምረው ከእነዚህ በአንደኛው ውስጥ ራስህን ታገኘው ከሆነ ንቃና ንስሃ ገብተህ መንገድህን አስተካክል።
3. ቁ7-9 ላይ እግዚአብሄር መስዋዕትን እንዳዘጋጀና ተጋባዦቹንም እንደቀደሰ ወይም እንደለየ ይነግረናል። ነብዩ ይህንን ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? በነዚህ ቁጥሮች ላይ ስንመለከት፤ በተለይም ቁ8 እግዚአብሄር ሊቀጣቸው ስለተዘጋጀው ሰዎች ማንነት ስንመለከት ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው?
4. ቁ10 ላይ "በዚያን ቀን" የሚለው አነጋገር የትኛውን ቀን ነው የሚያመለክተው? በዚያን ቀን ነብዩ ይሰማሉ ብሎ የሚናገራቸው ሶስት ዓይነት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑና፤ የሚሰሙበት ሥፍራም የት የት የት እንደሆነ በመዘርዘር ተናገር።
5. በቁ12 እና 13 ላይ እግዚአብሄር አምላክ እንደሚቀጣ የሚናገራቸው ምን ዓይነት ሰዎችን ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ "በዚያ ዘመን ኢየሩሳሌምን በመብራት እፈትሻለሁ።" እያለ ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? ከእግዚአብሄር ዓይን ሊሰወር የሚችል ፍጥረት ሊኖር እንደማይችል ምን ያህል ገብቶሃል?
6. የእግዚአብሄርን ቀን ብሎ ነብዩ የሚናገርለት ምን ዓይነት ቀን እንደሚሆን ለማስጠንቀቅ የተጠቀመባቸውን በቁ14-15 ውስጥ የተነገሩትን የተለያዩ ዓይነት መገለጫዎች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህን ቁጥሮች ስናነብ፤ ይህ የእግዚአብሄር ቀን አያለቅስም ወይም አይጮህም የሚባለውን ሰው እንኳን እንደሚያስለቅስና እንደሚያስጮህ የሚጠቁመንን ሃሳብ የት እናገኛለን?
7. ሰዎች በእግዚአብሄር ላይ ከሰሩት ሃጥያት የተነሳ እንደሚያመጣባቸው ከተናገራቸው መሃል በቁ17 ላይ የምናየው "እንደ እውር እንዲራመዱ በሰዎች ላይ ጭንቀት አመጣባቸዋለሁ" የሚለው ሃሳብ ምን ማለቱ ይመስልሃል? ቁ18 ላይ ነብዩ ሶፎንያስ በምን ዓይነት ሰዎች ላይ ነው ትኩርቱን አድርጎ ሲያስጠነቅቅ የምመለከተው?
8. ቁ5 ላይ እግዚአብሄር አጠፋለሁ ከሚላቸው ውስጥ ለእግዚአብሄር የሚሰግዱና በስሙ እየማሉ፤ በሌሎች አማልክትም ደግሞ የሚምሉ ሰዎች ነበሩ፤ ይህንን ወደ እኛ ዘመን ብታመጣው ከምን ዓይነት ሰዎች ጋራ ነው ሊዛመድ የሚችለው? አንተስ ከእግዚአብሄር ላይ አብረህ ልታስኬድ የምትሞክረው በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ነገር አለ ወይ? እግዚአብሄር ብቻኛ የአምላክነት ሥፍራውን ከማንም ጋራ ሊጋራ ስለማይወድ የሚገባውን ሙሉ በሙሉ ልንሰጠው ይገባናል።

# <u>ጥናት ሁለት ሶፎንያስ 2፡1-15</u>

የጥናት ዓላማ፡- ጽድቅን ማድረግና እግዚአብሄርን መፈለግ ሞኝነት በሚመስልበት ህብረተሰብ መሃልም የእግዚአብሄር ልጆች የጽድቅና የትህትናን፤ እግዚአብሄርን የመፈለግን ህይወት ችላ ካሉ፤ በሌሎች ላይ የሚመጣው ፍርድ እንደሚያገኛቸው ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እናንተ የምድር ትሁታን ሁሉ፤ ትዕዛዙን የምትፈጽሙ፤ እግዚአብሄትን እሹ፤ ጽድቅንና ትህትናን ፈልጉ፤ በእግዚአብሄር የቁጣ ቀን ትሰወሩ ይሆናል።" ሶፎ 2፡3

1. ትንቢተ ሶፎንያስ 2፡1-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 እና 2 ላይ እግዚአብሄር ሊፈርድባቸው ያሉትን ሕዝቦች ምን በማለት ነው የሚጠራቸው? በዚህ ሥፍራ ላይ ነብዩ እነዚህን ህዝቦች እንዲሰበሰቡና እንዲከማቹ ሲጣራ፤ ምን ለማድረግ ነው እየጋበዛቸው ያለው?
2. እግዚአብሄር አምላክ በቁ8-9 ላይ ስናነብ በሞዓባውያንና በአሞናውያን ላይ ሲቆጣ የምናየው ምን አደረጉ ብሎ ነው? እነዚህ ሁለት ነገሥታት በእግዚአብሄር ህዝብ ላይ ስላደረጉት ነገር እግዚአብሄር በእነርሱ ላይ ሊያመጣ ያለው ፍርድ ምን ይመስላል? በጠላታቸው ላይ ፈርዶ ህዝቡ የጠላቱን ሰፈር እንደወርስ ያደረገ እግዚአብሄር፤ ዛሬም ጠላታችንን ጥሎልን በድል እንድንራመድ ያስችለናል።
3. ከቁ10-11 ያለውን ክፍል ስንመለከት፤ ከላይ ያየናቸው ሁለቱ ነገስታት፤ ሞዓባዊያንና ዐሞናውያን ትዕቢተኛነታቸውን የገለጡበት መንገድ ምንድነው ብሎ ነው የሚናገረው? እነዚህን ቁጥሮች ስንመለከት፤ ይህ እግዚአብሄር በሁለቱ ነገስታት ላይ ሊወስድ ያለው የማያዳግም እርምጃ ለእስራኤል ታላቅ ደህንነትን ከማስገኘት ሌላ የሚያስገኘው ተጨማሪ ውጤት ምንድነው?
4. እግዚአብሄር በሞዓባውያንና በአሞናውያን ላይ ሊያደርግ ያለውን ከተናገረ በኋላ በቁ12-13 ላይ ደግሞ ያተኮረባቸው ሁለቱ ነገስታት እነማን ናቸው? በመዝሙረ ዳዊት 68፡31 ላይ "መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች።" የሚለውንና በብዙዎቻችን ዘንድ ታዋቂ ከሆነው ጥቅስ ጋራ ይህንን በሶፎ 2፡12 ላይ የተነገረውን ጎን ለጎን አድርገን ስንመለከት ምን ትምህርት ማግኘት የምንችል ይመስልሃል?
5. የነነዌ ከተማ መጨረሻዋ ምን እንደሚሆን በ14ትና በቁ15 ውስጥ አስደናቂ በሆነ ዝርዝር ሲናገር ይታያል። በተለይ ቁ14ት ላይ በከተማይቱ ላይ እንደሚሆኑ የተነገሩት ነገሮችን በመዘርዘር ተናገር።
6. በቁ15 ላይ እግዚአብሄር በነብዩ በኩል የነነዌን ከተማ ምን በማለት ነው የሚጠራት? "ታዲያ እንዴት የዱር አራዊት የሚመሰጉባት ባድማ ሆና ቀረች?" በማለት ነብዩ ሁኔታው ገና እንደሚሆን ነገር ሳይሆን የተፈጸመ ነገር አድርጎ ነው የሚናገረው፤ ለምንድነው ገና ወደፊት እንደሚሆን ነገር የተነገረው ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር በቃሉ የተናገረውንና ቃል የገባውን ነገር እኛ ይሆን ይሆን? ብለን የምንጠራጠረውና የምንጠይቀው ነገር ሊሆን አይገባም።
7. ወደ ቁ3 ተመልሰን ስንመለከት፤ ሰዎቹ ትሑታንና የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ የሚፈጽሙ መሆናቸውን እያወቀ፤ ለምንድነው እግዚአብሄር በዚያው ቁጥር ውስጥ እግዚአብሄርን እንዲሹ፣ ጽድቅንና ትህትናንም እንዲከታተሉ የሚመክራቸው? በሃጥያተኞች ቀንተህ በጽድቅ የመኖርን ነገር ችላ ለማለት ቃጥቶህ ያውቃል ወይ? አካባቢያችን ሁሉ ርኩሰትና ሃጥያትን በሚጠጡ ሰዎች የተሞላ እንኳን ቢሆን፤ እግዚአብሄር ግን በጽድቅና እግዚአብሄርን በመፈለግ እንድንበረታና እንድንቀጥል ይወዳል።

# ጥናት ሶስት ሶፎንያስ 3፡1-20

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ከምርኮ በኋላ የእስራኤልን ቅሬታ ወደ ገዛ ምድሩ በመለሰበት ወቅት ትዕቢተኞችን እንዳስወገደ ሁሉ፤ ዛሬም ቢሆን በየዋህነትና በትህትና ምህረቱን ከመቀበል ይልቅ በትዕቢታቸው ደስ የሚሰኙትን ሰዎች ከእርሱ ዘንድ የሚመጣውን በረከት ይካፈሉ ዘንድ ፈቃዱ እንዳልሆነ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በትዕቢታቸው የሚደሰቱትን ከዚያች ከተማ አስወግዳለሁና፤ ከእንግዲህ ወዲያ በቅዱስ ተራራዬ ላይ አትታበዩብኝም። በእግዚአብሄር ሥም የሚታመኑትን የዋሃንና ትሁታንን በመካከላችሁ አስቀራለሁ።" ሶፎ 3፡11-12

1. ትንቢተ ሶፎንያስ 3፡1-20 በአንድነት ይነበብ፡፡ ቍ1-2 ላይ ለከተማይቷ የሰጣት ሶስት ስሞች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። እነዚህ ሶስት የተሰጧት ስሞች ከአምላኳ ጋራ ያላትን ግንኙነት፣ ስለግል ህይወቷና፤ ከሌሎች ጋራ ባላት ግንኙነት ላይ ያተኮሩ ናቸው፤ እነዚህን ሃሳቦች ከስሞቿ ጋራ በማዛመድ ምን ማለት እንደሆነ ለማስረዳት ሞክር። ይህች ከተማ ደግሞ ሌሎች ሶስት ልታደርግ ፈቃደኛ ያልሆነቻቸው ባህርዮች ታሳያለች፤ እነዚህ ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. በከተማይቱ ላይ ከተናገረ በኋላ በቁ3-4 ደግሞ በከተማይቱ ባለ ሥልጣናትና፣ በእግዚአብሄር ቤት አገልጋዮች ላይ አተኩሮ እናያለን። ስልጣናቸውን እያነሳ የሚናገራቸው አራት አይነት ሰዎች እነማን ናቸው? ስለ እነዚህ ስለ እያንዳንዳቸው የሚያደርጉትን ክፋት በአጠቃላዩ ይናገራል፤ ለምንድነው እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ ማተኮሩን ትቶ ባለሥልጣኖች ወይም መሪዎች ላይ ማተኮር የወሰነው? በአንጻሩ በቁ5 ላይ ስለ እግዚአብሄር የሚናገራቸው ነገሮች ምንድናቸው?
3. ቁ5-7ትን ስናነብ ከላይ ከተማይቱ ተብላ በቁ1 ላይ የተነገረላት ከተማ ማን እንደሆነች ከእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚጠቁመን ክፍል አለ፤ ክፍሉ የትናውና ከተማይቱም ማን እንደምትባል ተናገር። በቁ6-8 ላይ እግዚአብሄር በሌሎች መንግሥታትና ላይ ያደረገው ነገር ለኢየሩሳሌም ትምህርት እንደሚሆናት ጠብቆ ነበረ፤ እነዚህን ቁጥሮች ስትመለከት፤ በሌሎቹ ላይ ሲሆን ያየችው ጥፋትና መደምሰስ ለእግዚአብሄር ከተማ ለኢየሩሳሌም ትምህርት ሆኗታል ወይ? አንተስ ከሌሎች ውድቀትና ጥፋት ምን ያህል ትምህርት ትቀስማለህ?
4. ከቁ9 ጀምረን ወደታች ስናነብ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያቀደው ትልቅና ለየት ያለ ነገር እንዳለ እንረዳለን። ቁ9 ሲጀምር "በዚያን ጊዜ" በማለት የጀመረው የትኛውን ጊዜ ሊያመለክተን ፈልጎ ነው ብለህ ታምናለህ? በቁ9 እና 10 ላይ ስትመለከት፤ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሄር ህዝብ ቅሬታዎች ላይ ይሆናሉ ብሎ የተናገራቸውን ቢያንስ ሶስት ዋና ዋና ነገሮች ተናገር።
5. በቁ11-12 ላይ እግዚአብሄር ራሱ ስለ ሁለት ዓይነት ሰዎች ሲናገር እናገኘዋለን፤ እነዚህ ሁለት ዓይነት ሰዎች የትኞቹ እንደሆኑ ተናገር። ቁ13-15ትን ስንመለከት እስራኤል እንድትዘምር፣ እልል እንድትልና እጅግ ደስ እንድትሰኝ ነብዩ ሶፎንያስ ይናገራል፤ እስራኤል ይህንን ዓይነት የደስታና የእልልታ ህይወት እንድትጀምር ነብዩ የሚሰጣት ምክንያት ምን ነበረ?
6. በቁ16-19 ላይ በእግዚአብሄርና በህዝቡ መካከል የሚታየው ግንኙነት ምን ይመስላል?
7. ነብዩ ሶፎንያስ በ1፡2 ላይ ትንቢቱን ሲያመጣ የጀመረበት ሃሳብ ምን የሚል ነበረ? በ3፡20 ላይ ደግሞ ነብዩ ትንቢቱን ሲያጠቃልል ምን በሚል ሃሳብ ሲዘጋ ነው የምናየው?
8. ምንም እንኳን በቁ20 ላይ እግዚአብሄር ህዝቡን መልሶ ወዳገራቸው እንደሚሰበስባቸው ቢናገርም፤ በቁ11 እና 12 ወደ ከተማዋ እንዳይመለሱ የተናገረላቸው ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? ትዕቢት በእግዚአብሄር ዘንድ ምን ያህል አፀያፊ ነገር እንደሆነ ይታይሃል ወይ? መጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሄር ምን ጊዜም ቢሆን ትዕቢተኞችን መቃወሙንና ለትሁታን ደግሞ ጸጋ መስጠቱ የማይቀር ነገረ እንደሆነ በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ያረጋግጥልናል።